በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

## ዓለም አቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕብረት (International Orthodox Tewahedo Alliance - IOTA) በቤተ ክርስቲያን ላይ ላለፉት 30 ዓመታት የደረሱ ጥቃቶችን የያዘ ሪፖርት ማወጣቱን አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለ2000 ዓመታት ሰውን ለድኅነት ለማብቃት ስትተጋ መኖሯ ከዘለዓለማዊ ሕይወት ባሻገር ጤናማ ለሆነ ምድራዊ ኑሮ የሚበጁ ተግባራትን ስታከናውን ኖራለች፡፡ በዚህም ከምእመናኗ በተጨማሪ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወሳኝና ጠቃሚ፣ በዓለም መለያ የሆኗቸውን ዕሴቶች ማስገኘት ችላለች። አገራችን በቅኝ ገዢዎች ላለመወረሯ ቀዳሚውን ሚና የተጫወተችውም እርሷ ናት። የሥነ-ምግባርና የሞራል ምንጭ በመሆን፣ ሀገሩን የሚወድ፣ በሕግና ሥርዓት የሚመራ ሥልጡን ማኅበረሰብ በመገንባት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ዓለም የሚመሰክረው ነው። የራሷ ቋንቋና ፊደል ያላት፣ ለሥልጣኔ፣ ለኪነ ጥበብ፣ ለሥነ-ልሳን፣ ለመልክዓ ምድር፣ ለደንና የተፈጥሮ ሀብት መጠበቅ፣ ለሥነ-ሕንጻ ምርምር የሚጠቅሙ መጻሕፍትን አበርክታለች፡፡

ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሁሉ አስተዋጾ ማበርከቷ ተረስቶ ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ረቂቅ እና ታቅዶበት የሚፈጸም፣ በመንግሥት ድጋፍ ያለውና የፖለቲካ ፓርቲዎችም ጭምር ሰፊ ሱታፌ የሚያድርጉበት ጥቃት እየተፈጸመባት ይገኛል። ብዙዎቹ ጥቃቶች የሚፈጸሙት በአክራሪ እስልምና ሲሆን አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በመንግሥት መዋቅር በተቀመጡ ፕሮቴስታንቶች ድጋፍ ይፈጸማሉ። በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት ማለትም በአሁኑ ወቅት ሃገሪቱን በማስተዳደር ላይ ያለው የብልጽግና ፓርቲ ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህ ኦርቶዶክስ ጠልነቱ የተለየ መንግስታዊ ፕሮጀክት ሁኖአል። ኦርቶድክሳዊ ወደ ስልጣን አካባቢ እንዳይደርስ ይደረጋል። በአሰቃቂ ሁኔታ መግደል፣ማሳደድ አካል ማጉደል፣ አብያተ ክርስቲናትን ማቃጠል፤ የሀሰት ትርክት መንዛት ወዘተ የዕለት ከዕለት ዜና ሁኗል። በቤተ ክርስቲያን፣ በካህናትና ምእመናኖቿ ላይ የደረሱት እጅግ ዘግናኝ ጥቃቶች በሚገባ ሰንዶ ማዘጋጀት ይገባል።

መቀመጫውን በሰሜን አሜሪካ ያደረገው ዓለም አቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕብረት (International Orthodox Tewahedo Alliance - IOTA) በተለየ መልኩ ከ2011 ዓ/ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሱ ያሉ ጉዳቶቸን ትኩረት አድርጎ ለዓለማቀፉ ማኅበረሰብ ሲያደርስ የቆየ ሲሆን በዚህ ዓመትም ላለፉት 30 ዓመታት የደረሱትን ጥቃቶች ለመጀመሪያ ጊዜ መረጃዎችን በማሰባሰብ "**ባለፉት ፴ ዓመታት ሰማዕታተ ክርስትና**" በሚል ይህንን ሪፖርት አዘጋጂቶ አቅርቧል። በቀጣይም ተመሳሳይ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለኦርቶዶክሳውያንና ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚያደርስ ይሆናል። በዚህ ዓመት የወጣው ሪፖርትም ይሁን በቀጣይ ጊዜያት የሚወጡ ተመሳሳይ ሪፖርቶች ዋና ዋና ዓላማዎች

1) ለሃይማኖታቸው መከራ የተቀበሉ ክርስቲያኖችን በመዘከር የደረሰባቸው መከራ የሃይማኖታቸው ፍሬ መሆኑን ለመጭው ትውልድ ለማሳወቅ
2) ለአንባብያንና ለተመራማሪዎች ትክክለኛ መረጃ ለማድረስ

3) በየጊዜው የሚፈጸሙ ጥቃቶች በመንግሥትም ሆነ በግል ብዙኃን መገናኛዎች በቂ ሽፋን ባለማግኘታቸውና ችግሮቹን ለማስወገድ በሚመለከታቸው አካላት የተሠሩ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎች ባለመኖራቸው ምክንያት በየጊዜ ችግሩ እየከፋ መሔዱን ለማሳየት።
4) በኦርቶዶክሳውያን ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ድንገተኛ ሳይሆኑ ታስቦባቸውና በሚገባ ታቅደው፣ መዋቅራዊ ድጋፍም አግኝተው የሚፈጸሙ መሆናቸውን ለማሳየት ነው።
5) ለወደፊቱ አጥፊዎች ተገቢ በሆነ የፍርድ አደባባይ ቀርበው ፍትህ እንዲሰጥ ማድረግ።

ሪፖርቱ መረጃዎችን በትክክል መዝግቦ መያዝ ከተጀመረበት በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1983 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2014 ዓ/ም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ሲሆን በአራት ክፍል ተከፍሎ የቀረበ ነው። ይህም 1) ከ1983 – 1989 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች 2) ከ1990 – 1999 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች 3) ከ2000 – 2009 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች እና 4) ከ2010 – 2014 ዓ/ም ድረስ የደረሱ ጥቃቶ ያካተተ ነው።

በመጨረሻም በሪፖርቱ ማጠቃለያ ላይ እንደተገለጸው በየጊዜው የሚከሠተውን እንዲህ ያለውን ችግር ለማስወገድ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ በየደረጃው በአገልግሎት ላይ የሚገኙ አካላት ጋር በመተባበር መሥራትና አውቀው የሚያጠፉትን የመንግሥት ባለስልጣናት በማጋለጥ በሕግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ከሚችሉ በሃገር ውስጥ ካሉ ተቋማትና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ተቋማት ጋር መረጃዎችን በማድረስ መስራት እንደምንፈልግ ለመግለጽ እንወዳለን።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን

**ዓለም አቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕብረት**

**International Orthodox Tewahedo Alliance - IOTA**